# “የኢትዮጵያ እና የአማራዉ ሕዝብ ጣላት ወያኔ ብቻ ነዉ:: ” ታጋይ ጌትነት አናጋዉ የአማራ ድሞክራሲዋ ሃይል ንቅናቄ ከፍተኛ አመራር

**Aseged Tamene (September 25, 2015)**

**https://freedom4ethiopian.wordpress.com/2015/09/25/dfer/**



ወያኔ ሀገራችን የነበራትን ስም ዝና እንዳልነበር ያደረገና ሌላ የእኛ ያልሆነች ኢትዮጵያን ለመፍጠር ታርኳንና ስሟን በመቀየር ያላደረገዉ ነገር የለም:: አሁንም በሙሉ አቅሙ እየሰራ ይገኛል:: ይሕ ማለት አለም አንቱ ያላቸዉን መሪዎቻችን ቅርሶቻችንን ባለቤት አሳጥቶቸዋል አፍርሶቻዋል አቃጥሎቸዋል:: ይሕም በቅርቡ እየሆነ ያለ እና እየተደረገ ያለ በመሆኑ ለሕዝባችን ግልፅ ነዉ:: በተለይ አማራውን ከሌሎች ወገኖቹ ጋር አብሮ ተከባብሮ እና ተፋቅሮ እንዳይኖር ወያኔ ሲመሰረት ጀምሮ ቁጥር አንድ ፕሮግራሙ አድርጎ ይዞት ከዚሕ ደርሶል:: ወያኔ በአማራዉ ሕዝብ ላይ የዘር ማጥፋትና ማፅዳት ማካሄድ የጀመረባቸዉ ግዜዎችና ቦታዎች በቅድ የተያዙ እና ቴክኒካል በመሆን የተፈጠሙ ናቸው:: ወያኔ አማራን ማፅዳት የጀመረዉ ከትግራይ ክፍለ ሐገር ሲሆን የመንግስት ሰራተኛ የነበሩትሙሉ በሙሉ ከትግራይ አማራን እንዲወጡ አድርጓል:: ከዚሕ በሓላ ወደ ጎንደር በ1971 ዓም ጀምሮ ጦርነቱን ሲያስፋፋ ወልቃይት ፀገዴ የሚኖሩ የጎንደር አማሮችን በጅምላ በመፍጀት ነበር:: እስከ ዛሬ ድረስ ምን ያሕል እንደተጨፈጨፉ ባይታወቅም ሰላሳ ሽ በላይ ከምድረ ገፅ ጠፍተዋል ከዘጠና ሽ በላይ ከቀያቸዉ ተፈናቅለዋል::

ስደተኛም ሑነዋል አካባቢዉን ሙሉ በሙሉ ለትግራይ አድርጓል:: ስልጣን ከያዘ በሓላ 1983 ዓም ጀምሮ አማራን ነፍጠኛ ትምክተኛ አድሃሬዎች ጨቋኞች የትግራይ ሕዝብ ደም መጣጮች እያለ ከሐገራቸዉ አፈናቅለዋል:: ለምሳሌ

1 በሀረር በበደኖ ግራዋ ሀብሩ

2 በአርሲ በአርባ ጉጉ እና ጢቶ

3 በወላይታ በከፋ በጉራ ፈርዳ በመተከል በአሶሳ በወለጋ በኤሊባቡር በባሌ በሲዳሞ በጌድዎ እና በሌሎች አካባቢዎች

በሙቶ ሺዎች የሚቆጠሩ አማራዎችን በአሰቃቂ ሑኔታ ፈጅተዋል:: ዉድ የሐገራችን ሕዝብ ይሕን የሐገር ና የሕዝብ ጠላት የሖነዉን በድን ጠራርገን ለማስወገድ ተደራጅተን ልንታገለዉ ይገባል::ወቅቱ አሑን ነዉ በተለይ መከራዉ እና ስቃዮ እንዲያበቃ የአማራ ሕዝብ ከአማራዉ ድርጅት ከአማራ ዲሞክራሳዊ ሃይል ንቅናቄ ጎን እንድትሰለፉ ጥሪያችን እናቀርባለን::

እናሸንፋለን